# PARKROSE PLAN

## MAKE OUR FUTURE BRIGHTER



DRAFT

የፓርክሮዝ የማህበረሰብ ዕቅድ

ኤፕሪል 2022

# የፓርክሮዝ የማህበረሰብ ዕቅድ ምንድን ነው?

**ለወደፊቱ የፓርክሮዝ ሁኔታ በዕቅዱ ላይ በጋራ እየሰራን ነው!**

የፓርክሮዝ መኖሪያ መንደር እያደጉ የመጡ የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶችን፣ የተለያዩ ህዝቦችና ባህሎችን፣ እና የአካባቢ ድርጅቶችን እና የንግድ ድርጅቶችን ጨምሮ ብዙ የማህበረሰብ ጠንካራ ጎኖች የሚገኙበት መጠነ ሰፊ የፖርትላንድ አካል ነው። ሆኖም፣ የኪራይ ዋጋ መጨመርን፣ ለተማሪዎችና ወላጆቻቸው ተጨማሪ የመኖሪያ የላብ ዋጋ የሚከፍሉ ስራዎች ማስፈለጋቸውን፣ በሳንዲ ቦሊቫርድ/Sandy Boulevard ያሉትን ምቹ ያልሆኑ ሁኔታዎችን፣ የማህበረሰብ መሰባሰቢያ ቦታዎች ማስፈለግን እና የአደጋ ዝግጁነት እቅድ ማስፈለግን ጨምሮ የፓርክሮዝ ማህበረሰብ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ ሌሎች ለረጅም ጊዜ ያልተፈቱ ችግሮችም አሉ።

የተለየ ቀለም ያላቸው ማህበረሰቦች እና በታሪክ ውስጥ የተገለሉ ቡድኖች በአብዛኛው የእነዚህ ተጽእኖዎች ከፍተኛ ተጎጂ ቢሆኑም ባለፉት ጊዜት ዕቅዶች ውስጥ ተሳትፏው በጣም ዝቅተኛ ነበር። በፖርትላንድ የዕቅድ ዝግጅትና ዘላቂነት (BPS) እና የኦሬጎን የትራንስፖርት መምሪያ ድጋፍ Historic Parkrose NPI ስለ ማህበረሰቡ ችግሮችና የመፍትሄ ሀሳቦች በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት በዝቅተኛ ደረጃ አገልግሎት ካገኙ ቡድኖች ጋር በጋራ በመሆን የፓርክሮዝ የማህበረሰብ ዕቅድን አዘጋጅቷል። የማህበረሰብ ተሳትፎ ተግባሮች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:

- ከመጋቢት እስከ ግንቦት 2021 ዓ.ም የተካሄዱት የወጣቶች ዓውደ ጥናቶች
- ከግንቢት እስከ ሰኔ 2021 ዓ.ም የተካሄዱት የማህበረሰብ ዓውደ ጥናቶች
- የመኖሪያ ቤት አልባ ወጣቶችን ሥነ ጥበብና ህልሞችን የሚያብራራ የፓርክሮዝ የፊልም ማጣሪያ
- የፓርክሮዝ የማህበረሰብ ዕቅድ ለማህበረሰብ ክፍት መኖሪያ ቤቶች
- የፓርክሮዝ የማህበረሰብ ዕቅድ የኦንላይን/በበየነ መረብ የዳሰሳ ጥናቶች

እ.ኤ.አ. በ2012 የተመሰረተው ታሪካዊ ፓርክሮዝ በፖርትላንድ ፓርክሮዝ ሰፈር ውስጥ ማህበራዊ ፍትሃዊነትን፣ ኢኮኖሚያዊ እድልን እና ደህንነትን ለማሳደግ ቁርጠኛ የሆነ የሰፈር ብልጽግና ተነሳሽነት (NPI) ነው።
ታሪካዊ ፓርክሮዝ ከ99ኛ እስከ 121ኛው በ Sandy Blvd ላይ በዒላማው አካባቢ ላሉ ንግዶች የመደብር የፊት ለፊት ማሻሻያ ስጦታ፣ የቴክኒክ ድጋፍ እና ድጋፍ ይሰጣል፣ እና በተለያዩ ጎረቤቶቻችን፣ በአከባቢ ንግዶች እና በንብረት ባለቤቶች መካከል ትብብርን ያበረታታል።

DRAFT

# የዕቅዱ ዓላማ

የፓርክሮዝ የማህበረሰብ ዕቅድ ዓላማ የፓርክሮዝ ማህበረሰብን እያጋጠሙ የሚገኙ ችግሮችን በመፍታት ረገድ ለሚረዱ ድርጊቶች ጥሪ ማቅረብ አለበት።  በተጨማሪም አላማው የማሕበረሰብ ጥንካሬዎችን ማጎልበት ነው፤ ለምሳሌ፡ የተለያዩ ባህሎቻችንን ማክበር፣ የአካባቢ የንግድ ድርጅቶችን መደገፍ እና ወጣቶቻችንን እንዲነሳሱ መደገፍ። እነዚህ እርምጃዎች እውን እንዲሆኑ በጥረቱ መግፋት የፓርክሮዝ ማህበረሰብ ኃላፊነት ነው።  ይሕ ዕቅድ በፓርክ ሮዝ የተዘጋጀ እና ለፓርክ ሮዝ የተዘጋጀ ነው።  ሁላችንም።

በቀጣዮቹ ገጾች ውስጥ፣ በአሳታፊ ተግባሮች ወቅት ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ስምምነት የተደረገባቸው ልዩ ርሰ ጉዳዮች ችግሮችና መፍትሄዎች ማጠቃለያን ያገኛሉ። ስለ እያንዳንዱ መፍትሔዎች ተጨማሪ ዝርዝሮችን የማግኘት ፍላጎት ካሉዎ **የፓርክሮዝ የማህበረሰብ ዕቅድን** ይመልከቱ ወይም የ Historic Parkrose ሰራተኛ ያነጋግሩ።

# የፓርክሮዝ የማህበረሰብ ዕቅድ ርዕሰ ጉዳዮች


**በተመጣጣኝ ዋጋ መኖሪያ ቤት ማቅረብና መፈናቀልን መከላከል**

ገጽ 5

**ለስራ ተደራሽነት / መኖሪያ ቤትን መሰረት ያደረጉ የንግድ ስራዎች እና አነስተኛ የንግድ ስራዎች**

ገጽ 7

**የሳንዲ ቦሊቫርድ/ Sandy Boulevard ደህንነት**

ገጽ 9

**የመኖሪያ መንደር የትራንስፖርት ፍላጎቶች**

ገጽ 11

**የማህበረሰብ ቦታዎችና ለተፈጥሮ ተደራሽ መሆን**

ገጽ 13

**የአስቸኳይ ጊዜ ዝግጁነት**

ገጽ 15


DRAFT



# Affordable Housing AND Anti-Displacement

# በተመጣጣኝ ዋጋ መኖሪያ ቤት ማቅረብና መፈናቀልን መከላከል

## ችግሮች

- ፓርክሮዝ ውስጥ የመኖሪያ ቤት ዋጋ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ወደ መንደሩ ከመምጣታቸው ጋር ተያይዞ የበለጠ እየተወደደ መጥቷል።
- ተከራዮች ለቤተሰባቸው አባላት ብዛት የሚመጥን የመኖሪያ ቤት ለማግኘት በጣም እየተቸገሩ በመሆናቸው ምክንያት ይህም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦችን እና የተለየ ቀለም ያላቸው ማህበረሰቦችን ከመኖሪያ መንደሩ እንዲፈናቀሉ እያደረገ ነው።
- ወደ 9 በመቶ ያክሉ የፓርክሮዝ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በ 2021-22 ዓ.ም የትምህርት አመት ውስጥ መኖሪያ ቤት አልባ፣ በዋናነትም ከዘመዶቻቸው ወይም ጓደኞቻቸው ጋር የሚኖሩ ነበሩ።
- ቤተሰቦች መረጋጋትና አለመፈናቀልን ይፈልጋሉ። ቤተሰቦች ለረጅም ጊዜ የሚቆዩበትና ለተለዋዋጭ ፍላጎቶቻቸው የሚመጥን ቦታ መኖር ይፈልጋሉ።

## መፍትሄዎች

የኪራይ ዋጋዎችን አቅም የሚፈቅዱ ለማድረግ ከመንግስት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ መኖሪያ ቤት ከሚያቀርቡ ቡድኖችና የግል የንብረት ባለቤቶች ጋር አብሮ መስራት፤ አዳዲስ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ መኖሪያ ቤቶችን ማቅረብ፣ ለቤተሰቦች የመኖሪያ ቤት ባለቤት የሚሆኑባቸውን ዕድሎች መፍጠር፣ የተለየ የቆዳ ቀለም ላላቸው ተከራዮችና መኖሪያ ቤት አልባ ቤተሰቦች ጥበቃ ማድረግ፣ እና መፈናቀልን መከላከል። ይህን ለማሳካት የሚወሰዱ እርምጃዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:

- ክፍት በሆኑ ቦታዎችና በፓርክሮዝ የትራንዚት ማዕከል አቅራቢያ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ መኖሪያ ቤቶችን መገንባት
- አሁን ያሉትን የአፓርታማ ህንጻዎች ተመጣጣኝ ዋጋቸውን ይዘው እንዲቀጩሉ ለማድረግ ከአጋሮች ጋር አብሮ መስራት
- በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ መኖሪያ ቤቶችን እንደ የ Rossi Farms መልሶ ልማት በመሳሰለ አዲስ ልማት ውስጥ ማካተት
- ለመኖሪያ ቤት አልባ ሰዎች አስተማማኝ መጠለያዎችን ማቅረብ
- እነዚህን መፍትሄዎች የሚተገብሩ ሰራተኞች መቅጠር

መፈናቀል ማለት ሰዎች ወይም የንግድ ድርጅቶች የአንድ የመኖሪያ መንደርን የኑሮ ሁኔታ መቋቋም ባለመቻላቸው ምክንያት ከመኖሪያ መንደሩ ለቀው ለመሄድ ሲገደዱ ነው። ይህ የሚሆነው በኢኮኖሚ ዕድሎች አጋጀች፣ የመኖሪያ ቤት ወጪዎች መጨመር፣ ወይም የመኖሪያ መንደሩን ዕቃዎችና አገልግሎቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት ላይ በሚደረጉ ለውጦች የተነሳ ሊሆን ይችላል።

DRAFT


Jobs And
Call Here!
Jobs 4 TEENS!
Jobs
Support small businesses
Home-based Business!

# ስራዎችን ተደራሽ ማድረግ

## ችግሮች

» ፓርክሮዝ ውስጥ የመካከለኛ ቤተሰብ ገቢ $15,000 ሆኖ በጠቅላላው ከፖርትላንድ ያነሰ ሲሆን የጥቁርና ሂስፓኒክ መካከለኛ ቤተሰቦች ገቢ ደግሞ $30,000 ሆኖ ከዚህም ያነሰ ነው

» የፓርክሮዝ ወጣቶች በአብዛኛው የስራዎችና ሙያዎች መንገዶቻቸውን እንዴት መጀመር እንዳለባቸው አያውቁም

» በቅርብ በሚገኘው የኮሎምቢያ ኮሪደር ስራ ቀጣሪ ዲስትሪክት ውስጥ ብዙ መካከለኛ የላብ ዋጋ ክፍያ የሚያስገኙ ስራዎች ያሉ ቢሆንም በአካባቢው ስራ የሚሰሩት ጥቂት የፓርክሮዝ ነዋሪዎች ብቻ ናቸው።

## መፍትሄዎች

ወጣቶችን በተለይም ተጠቃሚ ካልሆኑ የማህበረሰቡ አባላት የመጡ ወጣቶችን ለብልጽና መንገድ ሆነው ከሚያገለግሉ ስልጠናዎች፣ ስራዎችና ሙያዎች ጋር ማገናኘት። አዋቂ ሰዎች የመኖሪያ የላብ ዋጋ ክፍያ የሚከፍሉ ስራዎች የሚያገኙባቸው ማዕከላዊ ቦታዎች ማዘጋጀት እና ለወጣቶች ስልጠና የሚያገኙባቸው ዕድሎችን መፍጠር። ወጣቶችን ከስራ እድሎች ጋር በማገናኘት ከማህበረሰቡ አጋሮች ጋር ይስሩ፣ ለምሳሌ እንደ፡ -

» ልምምዶች፣ አማካሪዎች፣ የሙያ ምክር እና ለወጣቶች የስራ እድሎች

» የአምራች፣ የንግድ እና ከአየር ንብረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስራዎች ፍላጎት ላላቸው ወጣቶች የሚቀርቡ ፕሮግራሞች

» የተማሪዎች ቤተሰቦችን ከስራ ስልጠናና ድጋፍ ጋር የሚያገናኝ የትምህርት ቤት ድጋፍ

# መኖሪያ ቤትን መሰረት ያደረጉ የንግድ ድርጅቶችና አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች

## ችግሮች

» የፓርክሮዝ ነዋሪዎች Historic Parkrose Main Streetን አካባቢያዊ የንግድ ድርጅቶች የሚበቅሉበትና የሚያብቡበት እንዲሁም የመኖሪያ መንደሩን ብዝሀነት የሚያሳይ ቦታ እንዲሆን ይፈልጋሉ።

» የፓርክሮዝ ነዋሪዎች መኖሪያ ቤትን መሰረት ያደረጉ የንግድ ስራዎችን ለመጀመር ድጋፍ ማግኘት የሚፈልጉ ሲሆን አብዛኞቹ መኖሪያ ቤትን መሰረት ያደረጉ የንግድ ስራዎችን የሚሰሩ ነዋሪዎች ተጨማሪ ደንበኞችን ለመድረስ እርዳታ ይፈልጋሉ።

## መፍትሔዎች

ለአነስተኛ የንግድ ድርጅቶችና መኖሪያ ቤትን መሰረት ያደረጉ የንግድ ስራዎች በተለይም ባለቤቶቻቸው በአብዛኛው የንግድ ድርጅቶችን ለመጀመርና ለማሳደግ አጋጀች የሚያጋጥሟቸው ስደተኞች፣ ጥገኝነት ጠያቂዎችና ሌሎች የተለየ ቀለም ያላቸው ሰዎች ለሆኑ አነስተኛ የንግድ ድርጅቶችና መኖሪያ ቤትን መሰረት ያደረጉ የንግድ ስራዎች ድጋፍ ማድረግ። ይህን የሚያሳኩ ጥቂት ሀሳቦች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡

» መኖሪያ ቤትን መሰረት ላደረገ የንግድ ስራ ባለቤቶች አገልግሎቶችና ሀብቶችን ማቅረብ። አገልግሎቶች የቋንቋዎችና ባህሎች ብዝሀነትን ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማረጋገጥ

» ለተለያዩ የአነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ባለቤቶች የጋራ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ የኪራይ ቦታዎች ማዘጋጀት

» የአካባቢ የአነስተኛ የንግድ ድርጅት ባለቤቶችን በተለይም የተለየ የቆዳ ቀለም ያላቸው ባለቤቶችን ህልውና ለማስቀጠል እንደ የአርሷደሮች ገበያዎች፣ ተንቀሳቃሽ የገበያ ቦታዎች፣ ወዘተ የመሳሰሉ ቦታዎችን ማዘጋጀት።

» ለ Historic Parkrose Main Street የንግድ ስራዎች ድጋፍ ማድረግ

DRAFT


Sandy Boulevard Safety
BUS 21

# የሳንዲ ቦሌቫርድ ደህንነት

## ችግሮች

» ሳንዴ ቦሌቫርድ ለመኖሪያ ቦታዎች በእግር መንገድ ርቀት የሚገኙ ብዙ የንግድ ድርጅቶችና ሌሎች መዳረሻ ቦታዎች ያሉት ቢሆንም ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ መኖሩ እና ለደህንነት አስተማማኝ የእግረኛ ማቋረጫዎች ጥቂት መሆናቸው ሰዎችን በእግር እንዲጓዙ አያበረታቱም።

» በፓርክሮዝ ውስጥ ሳንዲ ቦሌቫርድ ከፍተኛ የመኪና ግጮቶች ከሚደርሱባቸው ቦታዎች መካከል አንዱ ሲሆን ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ ከ 300 በላይ ግጮቶች መድረሳቸው ሪፖርት ተደርጓል – አብዛኞቹ ከባድ ጉዳቶች በእግረኞች ላይ የደረሱ ናቸው

## መፍትሄዎች

ሳንዴ ቦሌቫርድን ለእግር መንገድ፣ ጉዞና የንግድ ስራ አስተማማኝ ቦታ የሚያደርጉ ማሻሻያዎችን ማስተዋወቅ የሚመከሩ ማሻሻያዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:

» የ NE 106th (በ Parkrose Hardware) እና በ NE 115th መንገድ ማቋረጫዎችን ማቋረጥን ቀላል ለማድረግ ተጨማሪ ምልክት የተደረገባቸው የእግረኛ ማቋረጫዎችን መጨመር።

» አደገኛ ማቋረጫዎችን ሁኔታ ማሻሻል

» የመንገድ መብራቶችን ደረጃ ማሳደግ

» የትራንዚት አገልግሎቶችን እና የአውቶቡስ ማቆሚያ ቦታዎችና ጣቢያዎችን በማሻሻል ወደ ቦታው በአውቶቡስ መድረስ ቀላል እንዲሆን ማድረግ።

DRAFT


Make Your Mark
(even if it's just putting your hands in wet cement)

# የመኖሪያ መንደር የትራንስፖርት ፍላጎቶች

## ችግሮች

- » ፓርክሮዝ በአብዛኞቹ መንገዶች ላይ የጎን የእግረኛ መንገድ አለመኖሩ፣ ብዙ ከፍተኛ የትራፊክ መጨናነቅ ያለባቸው መንገዶች መኖራቸው (ለምሳሌ፡ 102nd፣ Prescott፣ እና Fremont) እና የብስክሌት መገልገያዎች ጥቂት መሆናቸው የሰዎችን ወደ አካባቢ መዳረሻዎች በእግር ጉዞ ወይም በብስክሌት እሄዳለሁ ብሎ የማሰብ አቅም ገድቦታል።
- » በሞቃት የበጋ ቀናት ጥላ የሚገኝባቸው ዛፎች የሚገኙባቸው መንገዶች ጥቂት ናቸው። የፓርክሮዝ ማህበረሰብ የከተማ ተጽእኖዎችን ለመገደብና የበለጠ ለመኖሪያ አመቺ አካባቢ ለመፍጠር ተጨማሪ የመንገድ ዛፎችና ሌሎች አረንጓዴ ነገሮች ያስፈልጉታል።

## መፍትሄዎች

መንገዶችን ለሰዎች ወደ አካባቢ መዳረሻዎች በእግርና በብስክሌት ለመሄድ አስተማማኝና ቀላል በሚሆኑበት መልኩ ማሻሻል። የተመከሩ ማሻሻያዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:

- » የጎን መንገዶችና የእግረኛ ማቋረጫዎችን መገንባት እና መጨናነቅ በሚበዛባቸው መንገዶች ላይ በተለይም እንደ NE Shaver የመሰሰሉ ከትምህርት ቤቶች ጋር የሚያገናኙ መንገዶች ላይ ያሉትን መብራቶች ማሻሻል
- » ዝቅተኛ የትራፊክ ፍሰት ባለባቸው መንገዶች ላይ አስተማማኝና ለመድረስ ቀላል እንዲሆኑ ለማድረግ የብስክሌት መንገዶችን መጨመር ወይም ማሻሻል
- » እንደ የእግረኛ መንገድ ማሻሻያዎች አንድ ክፍል የመንገድ ዛፎችና አረንጓዴ እጽዋትን መጨመር
- » ከሳንዲ ቦሌቫርድ በስተ ሰሜን በኩል በቅርበት ከሚገኙ የስራ ቦታዎች ጋር የሚገናኙ የትራንዚት፣ የብስክሌትና የእግረኛ ማገናኛዎችን ማሻሻ

DRAFT


HA
HA
Rossi Farms
3839
Columbia
Slough

# የማህበረሰብ ቦታዎችና ለተፈጥሮ ተደራሽ መሆን

## ችግሮች

- ግማሽ ያክሉ የፓርክሮዝ ነዋሪዎች ከማህበረሰብ ፓርክ ከግማሽ ማይል በላይ ርቀት ይኖራሉ
- በቅርብ የሚገኘው የተፈጥሮ ቦታ ኮሎምቢያ ስላፍ ቢሆንም በመኖሪያ መንደሩ ውስጥ ምንም የህዝብ ወደዚህ መድረሻ ቦታዎች የሉም
- ወጣቶች ከትምህርት በኋላ የሚሄዱባቸው፣ የቤት ስራ የሚሰሩባቸው፣ በተግባሮች ላይ የሚሳተፉባቸው፣ እና ከስራዎችና የማህበረሰብ ዕድሎች ጋር የሚገናኙባቸው የማህበረሰብ ማዕከላት ወይም ሌሎች አስተማማኝ የማህበረሰብ ቦታዎች ማግኘት ይፈልጋሉ።

## መፍትሔዎች

ሰዎች የሚዝናኑባቸው፣ የሚሰባሰቡባቸው እና ለሚኖሩበት አካባቢ በቅርበት ተፈጥሮን የሚያገኙባቸው የማህበረሰብ ቦታዎች ማዘጋጀት። ይህን ለማሳካት የሚያስችሉ እርምጃዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:

- ለፓርክሮዝ ማህበረሰብ አዲስ ፓርክና የማህበረሰብ ማዕከል ስለሚሰራበት ሁኔታ ማመቻቸት
- ኮሎምቢያ ስላፍን ሰዎች ሄደው እንዲጠቀሙበት ማሻሻል
- በሳንዲ ቦሌቫርድ የንግድ ስራ ዲስትሪክት ወይም እንደ የ Rossi Farms ልማት አንድ ክፍል የማህበረሰብ መሰባሰቢያ ቦታዎችን ማዘጋጀት
- በመንገዶች ላይ ተጨማሪ ዛፎችና እጽዋቶች መትከል፣ እና የህዝብ መገኛ ቦታዎችን አረንጓዴነት ለመጠበቅ የማህበረሰብ ጽዳቶችን ማደራጀት።

DRAFT


Emergency kit
Ace Bandage
Antibiotic Ointment
BUTTERFLY
HYDROGEN PEROXIDE
BLANKET
GAUZE
ANTIBIOTIC
BANDAIDS
Emergency Power Here!
What Are Solar Power Benches?:
Solar power benches are a source of power within emergencies, that are available to everyone. Other things these benches have include:
1. Two USB ports
2. Wireless charging within acrylic glass
3. 4G Internet
4. Low environmental impact
And so much more!

# የአስቸኳይ ጊዜ ዝግጁነት

## ችግሮች

» የፓርክሮዝ ማህበረሰብ አባላት እንደ እጅግ ከፍተኛ ሙቀት ወይም ቅዝቃዜ፣ መብረቅ የሚያስከትል ብልጭታ ወይም ከፍተኛ ርዕደ መሬት ለመሳሰሉ ሊመጡ የሚችሉ ማንኛውም የድንገተኛ ጊዜ ሁኔታዎች መዘጋጀት አለባቸው።

» ብዙ የማህበረሰብ አባላት የድንገተኛ ጊዜ መጠቀሚያዎች ምን እንደሆኑ ወይም እነዚህን እንዴት እንደሚጠቀሙ፣ ሀይል በሚቋረጥበት ወቅት ሞባይል ስልኮቻቸውን ቻርጅ ለማድረግ የት እንደሚሄዱ ወይም በቀውስ ጊዜ በማህበረሰቡ ውስጥ ማን ጋር መሄድ እንዳለባቸው አያውቁም።

## መፍትሔዎች

ለፓርክሮዝ ማህበረሰብ የሚከተሉትን ጨምሮ በጋራ ሀብቶች እና የማህበረሰብ ዝግጁነትን የሚያሻሽሉ ድርጊቶች ላይ ተመስርቶ የአስቸኳይ ጊዜ ዝግጁነት ስትራቴጂ ማዘጋጀት፡

» የአስቸኳይ እንክብካቤ ማዕከላትን፣ የእሳት አደጋ ጣቢያዎች ማሻሻያዎችን፣ የድንገተኛ ጊዜ መረጃ ምልክቶችን፣ የመቀዝቀዣ/መሞቂያ መጠለያዎችን እና በሀይል መቋረጥ ወቅት የህዝብ የሀይል ማግኛ ምንጮችን ጨምሮ የአስቸኳይ ጊዜ መሰረተ ልማቶችን ማዘጋጀት።

» የካርቦን ልቀቶችን ለመጨመር የከተማ አረንጓዴ ቦታ ማዘጋጀት

» እንደ የአስቸኳይ ጊዜ ዝግጁነት እቅድ ያሉ የአስቸኳይ ጊዜ ግንኙነት ምንጮችን ማዘጋጀት እና እንደ የ Argay-Parkrose NET ቡድን የመሳሰሉ አሁን ያሉ የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎቶችን መደገፍ

» ጭንቀት ለሚያጋጥማቸው መኖሪያ መንደሮች ቀጣይ የሥነ ልቡና ድጋፍ አገልግሎቶችን የሚያቀርብ ኔትወርክ መፍጠር

DRAFT

# ምስጋና

## ማብራሪያዎች/ስዕሎች

### Say’Yonce Tate

ስሜ Say’Yonce Tate (Seance Tate) እና የ 17 ዓመት ዕድሜ ያለኝ የ 12ኛ ክፍል ተማሪ ልጃገረድ ስሆን በዚህ ዓመት (2022) እመረቃለሁ። እስከማስታውሰው ድረስ ቅልቅል የሚያ ኪነ ጥበብ የፈጠርኩ ሲሆን በሥነ ጥበብ ስራዬ አማካኝነት የማህበረሰብ ስሜት ለመፍጠር በመስራቴ እንደምቀጥል ተስፋ አደርጋለሁ። ለማህበረሰቤ የእይታ ተጽእኖ ፈጣሪዎችን በማቅረቤ እና እያደጉ የሚሄዱ ሀሳቦችን እውን በማድረጌ ደስተኛ ነኝ። የኪነ ጥበብ ስራዬን ትልቁን ድርሻ የሚወስደው ግልጽና ዝርዝር ግራፊክሶችን ለማቅረብ ፈጠራና የተነሳሽነት ምንጬ እንዲኖረኝ ያስቻለኝ ዘንድ ያለፉ ጊዜያት ተሞክሮዎችን መጠቀሜ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዙሪያችን ብዙ ነገሮች የተከሰቱ ቢሆንም ከራሳችን ማህበረሰቦች በመጀመር የአለማችንን ወቅታዊ ችግር ለመፍታት ድምጻችንን ማሰማትና ሀብቶቻችንን መጠቀም ይኖርብናል። አለማችንን አስተማማኝ በማድረግ፣ የተሟሉ የጥንቃቄና የመጠባበቂያ እቅዶችን በማዘጋጀት የማምን ሲሆን እነዚህ ሌሎች ሰዎችን በነዚህ ላይ እንዲሰሩ እንደሚረዷቸው አምናለሁ።

**CASHAPP: $plutopop | VENMO: @plutopop**

### Ben Torres

ስሜ Ben Torres፣ እና የ 15 ልጅ ስሆን የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ነኝ። አካባቢዬ ላይ ለውጥ ለማምጣት እየሞከርኩ ነው። በህይወት ዘመኔ በሙሉ የኖርኩት ፓርክሮዝ ውስጥ ሲሆን ብዙ ለውጦችንም አደጋዎችንም ያየሁ በመሆኑ ለማህበረሰቤ የድርሻዬን ማበርከት እፈልጋለሁ። በምችለው መንገድ ሁሉ በማህበረሰባችን ላይ ተጽእኖ ማሳደር እፈልጋለሁ። ከ 10 ዓመቴ ጀምሮ ቀለም የምቀባና ከዚያ በፊት ጀምሮ ደግሞ ስዕል እስል የነበረ በመሆኑ እነዚህን ስዕሎች በማጋራቴ እድለኛ ነኝ። ለኪነ ጥበብ በጠቅላላው ከፍተኛ ፍላጎት ያለኝ እና ይህን ለመሆን ባለው ከፍ ያለ አጋጅ ምክንያት አስቸጋሪ ቢሆንም ምን አይነት ኪነ ጥበብ እንደምሰራ ሊሰማኝ፣ ጠቃሚ መልዕክቶችንም ማስተላለፍ እችላለሁ ብዬ አስባለሁ። እዚህ የሚገኝ ማንኛውም ሰው እኔ ያገኘኋቸውን ተመሳሳይ ዕድሎች እንዲያገኝ እና የፓርክሮዝ ነዋሪዎች ለውጥ ለማምጣት ጥረት እያደረገ እንደሆነ በማወቅ የደህንነት ስሜት እንዲሰማው እፈልጋለሁ።

የተማሪ አስተባባሪ
**Lillyanne Pham**

የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች
**Seile Tekle (Historic Parkrose)**
**Leslie Lum እና Bill Cunningham (BPS)**

የሌይአውት/ አቀማመጥ ዲዛይን:
**Angie Martinez**

# የግንኙነት መረጃ

ስለ ዕቅዱ የተመለከቱ ተጨማሪ ዝርዝሮችን ለማግኘት **የፓርክሮዝ የማህበረሰብ ዕቅድ** ድረገጽን ይጎብኙ (በእንግሊዘኛ ብቻ)።

Historic Parkrose:
**info@historicparkrose.com**

Portland Bureau of Planning and Sustainability
**Bill.Cunningham@portlandoregon.gov**

ይህ ፕሮጀክት በከፊል ከትራንስፖርትና ዕድገት አስተዳደር Transportation and Growth Management (TGM) ፕሮግራም በሚገኝ እርዳታ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ሲሆን ፕሮግራሙ የኦሬጎን የትራንስፖርት መምሪያ እና የኦሬጎን የመሬት ጥበቃና ልማት መምሪያ የጋራ ፕሮግራም ነው። ይህ የ TGM እርዳታ በፌደራል Fixing America’s Surface የትራንስፖርት ሕግ (“FAST Act”)፣ የአካባቢ አስተዳደር እና የኦሬጎን ግዛት ፈንድ በከፊል የገንዘብ ድጋፍ ይደረግለታል።
የዚህ ሰነድ ይዘቶች የግድ የኦሬጎን ግዛትን አመለካከቶች ወይም ፖሊሲዎች መግለጽ አይጠበቅባቸውም።